የሰ/መ/ቁ. 56010

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ቃድሮ ኑሬ

2. ወ/ሮ ይባ ሄቦ

3. ቱሪ ዋሪቱ

4. ወ/ሮ ሃጆ ዱቤ

5. ከድር ቢፍቱ

6. ወ/ሮ ሽምሲያ ዓብዱልቃድር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩን መነሻ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ ሆኖ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ተይዞ የቀረበው ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ክሱ /ክርክሩ/ የጀመረው በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱ እንደተመለከተው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከባንኩ ገንዘብ በብድር የወሰዱ ናቸዉ፡፡ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ለብዱሩ አመላለስ የዋስትና ግዴታ ገብተዋል፡፡ ብድሩ የተወሰደው በ24-7-88 ዓ.ም በተፈረመው ውል እንደሆነ መመለስ የነበረበት በ24-7-89 ዓ.ም መሆኑን ተበዳሪዎች ገንዘቡን ለመመለስ ባለመቻላቸው አመልካች በዋስትና የያዘው የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት አስገምቶ ሐራጅ ማወጣቱን ፣ የሐራጅ ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊትም በ19-5-92 ዓ.ም ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ጽፎ የነበረ መሆኑን በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ አመልካች በቀረበው ግምት ብር 52,525.10 ቤቱን መረከቡን በመጨረሻም አመልካች በቀሪ የሚፈለገውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ በ21-2-2001 ዓ.ም ክስ መመስረቱን ክሱን የሰማው ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ወደሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች

ከማለፉ በፊት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች የብድሩን ገንዘብ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመክፈላቸው አመልካች በ92 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል፡፡ ሆኖም በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረትም ገንዘቡን ሊከፍሉ ባለመቻላቸው በዋስትና በያዘው ቤት ላይ በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት የሐራጅ ማስታወቂያ ያወጣ ቢሆንም ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ ለጉዳዩ አፈጻጸም አግባብ ባለው የሥነ -ሥርዓት ህግ መሠረት ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦአል፡፡ አመልካች ቤቱን የተረከበው ሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ስለመሆኑም በተጠሪዎች መልስ ጭምር ተረጋጋጦአል፡፡ አመልካች ቤቱን ቢረከብም በዚህ ረገድ ተከፈለ ሊባል የሚችለው ዕዳ በተጠሪዎች ላይ የሚፈለገውን አጠቃላይ ዕዳ የሚሸፍንለት ሆኖ ባለማግኘቱ ቀሪው ዕዳ እንዲከፈለው በመጠየቁ ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካች ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦ ቀሪ ዕዳ የሚፈልግ መሆኑን ባረጋገጠበት ጊዜ እና ክስ በመሰረተበት ቀን /ጊዜ/ መካከል ያለው ጊዜ ሲታሰብ አስር ዓመት አልሞላም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ስለመገንዘባቸው ከተሰጠው ብይን ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህም ሆኖ የይርጋውን ጊዜ ያሰሉት ብድሩ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በመሆኑ የአስር ዓመትን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች በዋስትና የያዘውን ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሸጦ ለብድሩ መክፈያ ከማድረጉ በፊት ያልተከፈለ ቀሪ የብድር ገንዘብ የሚኖር ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ይችል ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ በመጀመሪያ ማድረግ የነበረበትም በመያዣነት የያዘውን ቤት ሸጦ ገንዘቡን መሰብሰብ እንደመሆኑ አመልካቹ ይህንኑ ፈጽሞአል፡፡

ተጠሪዎችን ቀሪ የብድር ገንዘብ ይክፈሉኝ በማለት ሊከስ የሚችለው በእርግጥም ያልተከፈለ ቀሪ ዕዳ መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከያዘ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም በውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1846 ተደንግጎአል፡፡

አመልካች ለብድር ገንዘቡ አመላለስ ዋስትና እንዲሆን የያዘውን ቤት በግምቱ ልክ ከተረከበ በኋላ ቀሪ ዕዳ እንደሚፈልግ እርግጠኛ የሆነው ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በተጠሪዎች ላይ ክስ መመስረት የሚችለው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረውም ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለው ሲታሰብ ጊዜው አላለፈበትም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከዚህ አንጻር ሲታይም በህጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04301 መስከረም 21 ቀን 2002 የሰጠው ብይን እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 77420 መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ በመሆኑም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በክሱ ስረ ነገር ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

# የዳኝነት
# ስልጣን